የሰበር መ/ቁ.21939

ቀን ሐምሌ 12/98

ዳኞች፡- 1- አቶ ፍሠሀ ወርቅነህ

2- አቶ ጌታቸው ምህረቱ

3- አቶ አሰግድ ጋሻው

4- አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5- ወ/ት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡- ኪንግናም ኢንተርፕራይዝ ሊሚትድ -ነ/ፈጅ ተስፋዬ ደገፋ

መልስ ሰጭ፡- አቶ አክሊሉ በቀለ - ቀረቡ

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር አንድ ሰራተኛ ከስራ የተሰናበተው በህገወጥ መንገድ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ስራ እንዲመለስ በአዋጅ ቁ.42/85 መሰረት ሲወሰን ከስራ ከተሰናበተበት ጊዜ ጀምሮ ወደ ስራ እንዲመለስ ውሳኔ እስክተሰጠበትና ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ ሊከፈለው ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ነጥብ የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የስር ፍ/ቤት መ/ሰጭ ከስራ የተሰናበተው በህገወጥ መንገድ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ስራው እንዲመለስ የወሰነ ሲሆን ውሳኔውን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም አጽንቶታል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት መ/ሰጭ መልሱን አቅርቧል፡፡

ለችሎቱም አንድ ሰራተኛ ከስራ የተሰናበተው በህገወጥ መንገድ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ስራ እንዲመለስ በአዋጅ ቁ.42/85 መሰረት ሲወሰን ከስራ ከተሰናበተት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 19-11-98

ጊዜ ጀምሮ ወደ ስራ እንዲመለስ ውሳኔ እስከተሰጠበትና ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ ሊከፈለው ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ አግባብነት ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ መርምሮታል፡፡

ይህ ችሎት በመ/ቁ.17189 አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁ.42/85ን ድንጋጌዎች በመተርጎም ህጉ ስራ ላልተሰራበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የሚፈቅድ አይደለም የሚል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ለመ/ሰጭ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

- ይህ ችሎት መ/ሰጭ ውዝፍ ደመወዙ ሊከፈል አይገባም በማለት ወስኖ የኦሮሚያ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመ/ቁ.463/01/96 ሚያዝያ 19 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ.09977 ህዳር 06 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት